መልእክት ሁለት

## የኤርሚያስ መጽሐፍ ማዕከላዊው እና ዋናው ነገር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 2፥13፤ 17፥9፤ 13፥23፤ 23፥5-6፤ 33፥16፤ 31፥33-34

**I. የኤርሚያስ መጽሐፍ ማዕከላዊው እና ዋናው ነገር ሦስት ነገሮችን ያካትታል—እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ነገር፣ በወደቀው ሁኔታችን ምን እንደሆንን እና ክርስቶስ ለእኛ ምን እንደሆነ፤ እነዚህን ሦስት ነገሮች ለማየት የኤርሚያስን የውጪ ሽፋን "ከፈት" ማድረግና ውስጡ ያለው ማዕከላዊው እና ዋናው ነገር ያም የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ትምህርት ላይ ማተኮር አለብን።**

**II. እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ነገር በዋናነት አምላካችን የሕያው ውኃ ምንጭ መሆኑን በሚገልጠው በኤርሚያስ 2፥13 ተገልጧል፦**

ሀ. እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ውጥኑ ለድሰታችን ያረካን ዘንድ የሕያው ውኃ መፍለቂያው፣ ምንጩ መሆን ነው፤ እርሱን እንደ የማንነታችን ምንጭ፣ መፍለቂያ እንድንወስደው ይፈልጋል፤ እግዚአብሔርን እንደ ሕያው ውኃ መፍለቂያ የምንወስድበት ብቸኛው መንገድ እርሱን ዕለት በዕለት መጠጣት ነው—ቁ. 13፤ 1 ቆሮ. 12፥13፤ ሮሜ 11፥36፦

1. ይህ የጌታን ስም ባለማቋረጥ መጥራትን (ከምስጋና፣ ከደስታ፣ ከጸሎትና ከውዳሴ ጋር) እና እንደ ሕያው ውኃ መፍለቂያ ከእርሱ በደስታ ውኃ መቅዳትን ከእኛ ይጠይቃል—ኢሳ. 12፥3-34፤ ዮሐ. 4፥10፣ 14፤ ሮሜ 10፥12፤ 1 ተሰ. 5፥16-18፤ 4፥3።
2. ኢሳይያስ 12፥3 እግዚአብሔርን እንደ መዳናችን መቀበያው መንገድ ውኃን ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ መቅዳት ያም እርሱን መጠጣት እንደሆነ ያሳያል—መዝ. 36፥8፤ ዮሐ. 4፥14፤ 7፥37፤ 1 ቆሮ. 12፥13፤ ራእ. 22፥17፤ 1 ዜና. 16፥8፤ መዝ. 105፥1፤ 116፥1-4፣ 12-13፣ 17፦

    ሀ. መዳናችን ለመሆን ሦስታንዱ አምላክ እንደ ሕያው ውኃ፣ እንደ የሕይወት ውኃ ሕይወትን-የሚሰጠው መንፈስ ለመሆን በሂደት አልፏል፤ የእግዚአብሔር ተግባራዊ ማዳን በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ራሱ እንደ ሕይወት ውኃ ነው—1 ቆሮ. 15፥45፤ ዮሐ. 7፥37-39፤ ራእ. 7፥17፤ 21፥6፤ 22፥1፣ 17።

    ለ. መፍለቂያው ምንጩ ነው፣ ከምንጩ የሚወጣው ፍልቁ ደግሞ መፍለቁ ነው፣ ወንዙ ደግሞ ፍሰቱ ነው፤ *የመድኃኒት ምንጮች* የሚለው ቃል የሚያመለክተው መዳን ምንጩ እንደሆነ ነው፤ መዳናችን የሆነው እግዚአብሔር ምንጩ ነው (ኢሳ. 12፥2)፣ ለድሰታችን እና ለልምምዳችን ክርስቶስ ፍልቁ ነው (ዮሐ. 4፥14)፣ መንፈስ የዚህ መዳን በእኛ ውስጥ መፍሰስ ነው (ዮሐ. 7፥38-39)።

    ሐ. መዳንን ለመደሰት ጌታ ራሱ መዳናችን፣ ብርታታችን እና መዝሙራችን መሆኑን እና ስሙን በመጥራት ከመድኃኒት ምንጮች ውኃን በደስታ መቅዳት እንደምንችል መገንዘብ ያስፈልገናል—ኢሳ. 12፥2-3።

    መ. ከመለኮታዊው ማዳን ምንጮች ውኃ መቅጃው መንገድ ንስሐን፣ መጥራትን፣ መዘመርን፣ ማመስገንን፣ ማወደስን እና የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ማስታወቅን ያካትታል—ቁ. 4-6።

ለ. ሕያው ውኃ ውስጣችን ሲገባ፣ እኛ እንድንመገብ፣ እንድንለወጥ፣ እንድንመስል እና እንድንከብር ለማድረግ ወደ እኛ ዘልቆ ይገባል፣ በመላው ማንነታችን ያልፋል፣ ከእኛ ጋር ይዋሐዳል—ቁ. 3፤ ዮሐ. 4፥10፣ 14፤ ሮሜ 12፥2፤ 8፥29-30።

ሐ. "እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ"—ዮሐ. 4፥14፦

1. ሦስታንዱ አምላክ በመለኮታዊው ሥላሴ በሦስት ደረጃዎች ይፈስሳል፦ አብ መፍለቂያው ነው፣ ወልድ ፍልቁ ነው፣ መንፈስ ወንዙ ነው።
2. የሦስታንዱ አምላክ መፍሰስ "ለዘላለም ሕይወት" ነው፦

    ሀ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የዘላለም ሕይወት ጥቅል-ድምር ናት፣ ለ የሚለው ቃል "ለመሆን" ማለት ነው፤ ስለዚህ፣ *ለዘላለም ሕይወት* ማለት የዘላለም ሕይወት ጥቅል-ድምር ያም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሆን ማለት ነው።

    ለ. ሕያዉን ውኃ በመጠጣት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ የዘላለም ሕይወት ጥቅል-ድምር፣ የሚፈስሰው ሦስታንዱ አምላክ መዳረሻ እንሆናለን።

መ. የሕያው ውኃ መፍለቂያ በመሆኑ ያለው የእግዚአብሔር ግብ ለመገለጡ እንደ እርሱ መጨመር ሙላቱ ትሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን ማፍራት ነው፤ ይህ እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ያለው የልብ ፍላጎት፣ በጎ ደስታው ነው—ኤር. 2፥13፤ ሰቆ. 3፥22-24፤ 1 ቆሮ. 1፥9፤ ኤፌ. 1፥5፣ 9፣ 22-23።

ሠ. የሕያው ውኃ መፍለቂያ ከሆነው ከእግዚአብሔር ውጪ ምንም ነገር ጥማችንን ሊቆርጥና ሊያረካን አይችልም፤ ከእግዚአብሔር ወደ ውስጣችን መታደል ውጪ ምንም ነገር ለመገለጡ የእርሱ መጨመር ሊያደርገን አይችልም—ራእ. 22፡1፣ 17።

ረ. የእግዚአብሔር ሕዝብ የሕይወት መንፈስ እንደ ሕይወት ውኃ ባጠራቸው ጊዜ ሁሉ ችግሮች ይኖሩባቸዋል፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተትረፈረፈ የሚያድነው መንፈስ እንደ ሕይወት ውኃ ሲኖራቸው በመካከላቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ችግሮች ይቀረፋሉ—ዘጸ. 17፡1-7፤ ዘኍ. 20፡2-13።

## III. ሌላኛው የኤርሚያስ መጽሐፍ ማዕከላዊው እና ዋናው ገጽታ እኛ በወደቀው ሁኔታችን የሆንነውን ያጋልጣል፡-

ሀ. "የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?"—ኤር 17፡9፡-

1. የሰው ልብ አታላይ እና የማይድን መሆኑን የሚያመለክተው ይህ ቃል እንኳን በእደላው ከሆነው ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር የተዛመደ ነው፤ ምንም እንኳን የሰው ልብ ብልሹና አታላይ ሁኔታውም የማይድን ቢሆንም እንዲህ ያለው ልብ እግዚአብሔር የሕይወቱን ሕግ የሚጽፍበት ጽላት መሆን ይችላል—31፡33፤ ተዛ. 2 ቆሮ 3፡3።
2. ይህ እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ ራሱን ለመጨመር መንገድ እንዳለው ይገልጣል፤ እግዚአብሔር አንዴ ሰው ውስጥ ከገባ ከሰው መንፈስ ወደ ልቡ ውስጥ ይሰራጫል፤ ይህ በኢኮኖሚው መሠረት የወደቀውን ሰው ልብ የሚያተካክልበት የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

ለ. "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ"—ኤር 13፡23፡-

1. ምንጩን እና የሕይወት ውኃ መፍለቂያ የሆነውን እግዚአብሔርን በመተው (ኤር. 2፡13)፣ እስራኤል ክፉ ሆነ፣ ልክ መቀየር እንደማይችለው የኢትዮጵያዊ መልክና የነብር ዝንጕርጕርነት የማይለወጥ የኃጢአተኛ ባሕርይ ኖረው፤ ይህ የወደቀውን ሰው እውነተኛ ሁኔታ ያጋልጣል።
2. እንደወደቁ ሰዎች በራሳችን ውስጥ፣ በራሳችንና ከራሳችን የማንድንና የማንለወጥ ነን—ሮሜ 7፡18፤ ማቴ. 12፡34-35፤ 15፡7-11፣ 18-20፤ 1 ዜና. 28፡9፤ ተዛ. ሕዝ. 36፡26-27፤ ኤር. 32፡39-40።

ሐ. ጌታ በክብሩ ያለውን ራእይ በእውነት ያየ ሰው ሁሉ ርኩስ ስለመሆኑ በሕሊናው ውስጥ ይበራለታል፤ ስለራሳችን ምን ያህል መረዳት አለን የሚለው የሚወሰነው ጌታን ምን ያህል አይተነዋል በሚለው ልክ ነው—ኢሳ. 6፡5፤ ዮሐ. 12፡41፤ ኢዮ. 42፡5-6፤ ተዛ. ሉቃ. 5፡8፡-

1. ጌታን የበለጠ ባየነውና በተጋለጥን ቁጥር የበለጠ እንነጻለን፤ ከጌታ ጋር ያለን ኅብረት ባለማቋረጥ በጌታ ደም በመታጠብ መጠበቅ አለበት—1 ዮሐ. 1፡7፣9።
2. በአዲስ ኪዳን አውድ መሠረት እግዚአብሔርን ማየት ማለት በግል ልምምዳችን እግዚአብሔርን ከማግኘት ጋር እኩል ነው፤ እግዚአብሔርን ማግኘት ማለት በሕይወትና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እርሱን እንሆን ዘንድ በንጥረ-ነገሩ፣ በሕይወቱ እና በባሕሪው እግዚአብሔርን መቀበል ነው።
3. እግዚአብሔርን ማየት ይለውጠናል (2 ቆሮ. 3፡16፣ 18፤ ማቴ. 5፡8) ምክንያቱም እግዚአብሔርን በማየት የእርሱን ንጥረ-ነገር ወደ ውስጣችን እንቀበላለን፣ አሮጌው ንጥረ-ነገራችንም ከውስጣችን ይወገዳል፤ እግዚአብሔርን ማየት ማለት እግዚአብሔርን በሕይወቱ እንድንገልጠውና በስልጣኑ እንድንወክለው ክቡር ወደሆነው ወደ ክርስቶስ፣ ወደ አምላክ-ሰዉ መልክ መለወጥ ነው።
4. ወደ እርሱ የምንመለከተው አምላክ ራሱ ዛሬ የተጠናቀቀው መንፈስ ነው፣ በመንፈሳችን ወደ እርሱ መመልከት እንችላለን፤ በማለዳ ማነቃቂያችን ያለን ሰዓት አሥራ አምስት ወይም ሀያ ደቂቃዎች ብቻ ቢሆንም እንኳን፣ ከጌታ ጋር ለመሆን እና በመንፈስ ውስጥ ለመቆየት ጊዜ አለን።
5. ቃሉን እየጸለዩ-ማንበብ፣ ከእርሱ ጋር ማውራትና በአጫጭር ጸሎቶች ወደ እርሱ መጸለይ እንችላለን፤ ከዚያም ከእግዚአብሔር የሆነ ንጥረ-ነገር እየተቀበልን እንደሆነና ወደ ማንነታችን የእግዚአብሔርን ብልጥግናዎች እየመጠጥን እንደሆነ ይሰማናል፤ በዚህ መንገድ ዕለት በዕለት በመለኮታዊው መለወጥ እንለወጣለን፤ ይህ ሙሉ በሙሉ የሚሆነው እንደመንፈስ ወደተጠናቀቀው አምላክ በመንፈሳችን በመመልከት ነው።
6. እግዚአብሔርን የበለጠ ባየነው፣ ባወቅነውና በወደድነው ቁጥር፣ የበለጠ ራሳችንን እንጸየፋለን፣ የበለጠም ራሳችንን እንክዳለን—ኢዮ. 42፡6፤ ማቴ. 16፡24፤ ሉቃ. 9፡23፤ 14፡26።

## IV. በኤርሚያስ መጽሐፍ ማዕከላዊው እና ዋናው ነገር ውስጥ ያለው ሦስተኛው ጉዳይ ክርስቶስ ለእኛ ምን እንደሆነ ነው፡-

ሀ. "እነሆ፣ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፣ ይላል እግዚአብሔር...የሚጠራበትም ስም እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው"—23፡5-6፤ ተዛ. 33፡16፡-

1. *እግዚአብሔር ጽድቃችን* የሚለው የሚያመለክተው ክርስቶስን በመለኮትነቱ ሲሆን *ጻድቅ ቍጥቋጥ* የሚለው ደግሞ ክርስቶስን በሰብእናው ያመለክታል።
2. እዚህ ጋር ያለው ስም፣ እግዚአብሔር ጽድቃችን የሚለው ክርስቶስ እንደ ዳዊት ዘር እንዲሁ ሰው ብቻ ሳይሆን ሰማይና ምድርን የፈጠረው፣ አብርሃምን የጠራው፣ የእስራኤልን ዘር ያጸናው፣ የዳዊት ጌታ የሆነው፣ ዳዊት ጌታ ብሎ የጠራው (ማቴ. 22፡42-45፤ ተዛ. ራእ. 5፡5፤ 22፡16) ያሕዌ ራሱን ያመለክታል፤ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጽድቅ ይሆን ዘንድ (1 ቆሮ. 1፡30) ያሕዌ ራሱ (የዳዊት ጌታ) እንደ ዳዊት ዘር (የዳዊት ልጅ) መጣ።
   ሀ. በቤዛነቱ መሠረት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል በክርስቶስ ማመን እንችላለን (ሐዋ. 10፡43)፣ እግዚአብሔርም ሊያጸድቀን (ሮሜ 3፡24፣ 26) እና ክርስቶስን እንደ ጽድቅ መጎናጸፊያ ሊያለብሰን ይችላል (ኢሳ. 61፡10)።
   ለ. ይህ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም የሥስታንዱ አምላክ አካል መልበስ ለሆነው ክርስቶስ (ቆላ. 2፡9) እንደ ሕይወታችን (3፡4)፣ በውስጥ እንዳለው የሕይወት ሕግ (ኤር. 31፡33) እና እንደ ሁሉ ነገራችን ራሱን ወደ መላው ማንነታችን ለማደል መንገድን ይሰጠዋል።

ለ. ክርስቶስ ራሱ በእግዚአብሔር የተሰጠን የሕይወት አዲሱ ኪዳናችን ነው—ኢሳ. 42፡6፤ 49፡8፤ ኤር. 31፡31-34፤ ዕብ. 8፡8-12

1. በግሪኩ ቋንቋ *ኪዳን* (covenant) እና *ኪዳን* (testament) ለሚሉት ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል፦
   ሀ. ኪዳን (covenant) እና ኪዳን (testament) አንድ አይነት ናቸው፣ ነገር ግን የኪዳኑ ፈጻሚ በሕይወት ካለ ኪዳን (covenant) ነው፤ ሲሞት ግን ኪዳን (testament) ነው፤ በዛሬው ቋንቋ ኪዳን (testament) ማለት ኑዛዜ ነው።
   ለ. ኪዳን (covenant ) ቃል ለተገባላቸው ሰዎች የሆነን ነገር ለመፈጸም የተወሰኑ ቃል ኪዳኖችን ያካተተ ስምምነት ሲሆን፣ ኪዳን (testament) ደግሞ ለወራሹ እንዲሰጡ የተወሰኑ ነገሮችን የያዘ ኑዛዜ ነው—9፡16-17፤ ተዛ. ዘዳ. 11፡29፤ 28፡1፣ 15፤ ኤር. 31፡31-32።
2. የሕግ የሆነው ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው ነገር ግን የጸጋው አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ማንነት ነው—ዮሐ. 1፡16-17፦
   ሀ. በክርስቶስ ስናምን የዚህ ምሳሌ ማንነት ወደ እኛ ውስጥ ይመጣል፣ በመንፈስ ስንመላለስና አእምሮአችንን መንፈስ ላይ ስናደርግ የሕግን የጽድቅ ጥያቄዎች በእኛ ይፈጽመዋል—ሕዝ. 36፡26-27፤ ሮሜ 8፡2፣ 4፣ 6፣ 10።
   ለ. ክርስቶስ በሞቱ በሕጉ መሠረት የእግዚአብሔርን የጽድቅ ጥያቄ አሟልቶ አዲሱን ኪዳን አጽንቷል (6፡23፤ 3፡21፤ 10፡3-4፤ ሉቃ. 22፡20፤ ዕብ. 9፡16-17)፣ በትንሣኤው ደግሞ ከነውርስ ኑዛዜዎቹ አዲስ ኪዳን ሆኗል (1 ቆሮ. 15፡45፤ ኢሳ. 42፡6፤ ፊልጵ. 1፡19)።
   ሐ. በዕርገቱ ክርስቶስ ስለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የሆነውን የአዲስ ኪዳን ማኅተም ፈታ፣ በሰማያዊው አገልግሎቱ ደግሞ እንደ መካከለኛው፣ እንደ ፈጻሚው ይዘቶቹን እየፈጸመ ነው—ራእ 5፡1-5፤ ዕብ 8፡6፤ 9፡15፤ 12፡24።
   መ. ከይሁዳ ነገድ እንደሆነው አንበሳ ሰይጣንን ድል-ነሥቶ አሸንፎታል፣ እንደ ሚቤዠው በግ ክርስቶስ የወደቀውን ሰው ኃጢአትና ኃጢአቶች አስወግዷል፣ እንደ ሰባቱ መናፍስት ክርስቶስ እንደ አዲስ ኪዳን ይዘቶች በራሱ ይሰርጸናል—ራእ. 5፡5-6፤ ዮሐ. 1፡29።
   ሠ. የእግዚአብሔር ማዳን፣ የእግዚአብሔር በረከቶች እና የእግዚአብሔር ብልጥግናዎች ሁሉ ለእኛ ቃል ተገብተዋል፣ ይህም ቃል ኪዳን ክርስቶስ ነው፤ በሙቶዎች የሚቆጠሩት በአዲስ ኪዳን ያሉት የውርስ ኑዛዜዎች ሁሉ እውነታ ክርስቶስ ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደ መንፈስ ራሱን ለእኛ ተናዟል—ዘፍ. 22፡18፤ ገላ. 3፡14፤ 1 ቆሮ. 1፡30፤ 15፡45፤ ኤፌ. 1፡3፤ 3፡8፤ ዮሐ. 20፡22።
3. መንፈሳችን የአዲሱ ኪዳን የውርስ ኑዛዜዎች ሁሉ "የባንክ ሂሳብ" ነው፤ በሕይወት መንፈስ ሕግ እነዚህ ሁሉ ወደ ውስጣችን ይታደላሉ ለእኛም እውን ይሆናሉ—ሮሜ 8፡2፣ 10፣ 6፣ 11፣ 16፤ ዕብ. 8፡10፤ ዮሐ. 16፡13።
4. የአዲሱ ኪዳን ማዕከል፣ ይዘት እና እውነታ የውስጡ የሕይወት ሕግ ነው (ሮሜ 8፡2)፤ በውስጣዊ ይዘቱ ይህ ሕግ መለኮታዊውን ሕይወት ያመለክታል፣ መለኮታዊው ሕይወት ሁሉን-ባካተተው ክርስቶስ አካል የለበሰው እና ሕይወትን በሚሰጠው መንፈስ እውን የሆነው ሦስታንዱ አምላክ ነው (ቆላ. 2፡9፣ 1 ቆሮ. 15፡45)፤ እርሱ ለመረጣቸው ሕዝቦቹ ሁሉ ነገር ለመሆን በሂደት አልፏል ተጠናቅቋልም፦
   ሀ. በአዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን እንደ ሕይወታቸው ወደ መረጣቸው ሕዝቦቹ ውስጥ ጨምሯል፣ ይህም ሕይወት ቅጽበታዊ ኃይል እና ሰው የማይቆጣጠረው መርህ ነው—ዕብ. 8፡10፤ ሮሜ 8፡2።

ሰ. በሕይወቱ መሠረት የአዲሱ ኪዳን ሕግ በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ነው፣ በአገልግሎቱ (በሥራው) መሠረት ሁሉን ቻዩ መለኮታዊ አቅም ነው፤ ይህ አቅም የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለማከናወን ሁሉን ነገር በእኛ ውስጥ ለማድረግ ይችላል።

ሐ. በውስጣዊ ይዘቱ ይህ ሕግ እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደ መንፈስ ነው፣ በአገልግሎቱ እኛን መለኮት የማድረግ አቅም አለው (ቁ. 2፣ 10፣ 6፣ 11፣ 28-29)፤ ከዚህም በተጨማሪ የውስጣዊው የሕይወት ሕግ አቅም ከልዩ ልዩ አገልግሎቶች ጋር (ሮሜ 12፡3-8፤ ኤፌ. 4፡11፣ 16) የክርስቶስ አካል ብልቶች አድርጎ ያቀናብረናል (1 ቆሮ. 12፡27፤ ኤፌ. 5፡30)።

መ. የሕይወት ሕግ በልባችን ላይ መጻፍ፣ መለኮታዊው ሕይወት የማንነታችን ማዕከል ከሆነው ከመንፈሳችን የማንነታችን ዳርቻ ወደሆነው ልባችን ስለመሰራጨቱ ከሆነው የአዲስ ኪዳን ትምህርት ጋር የተዛመደ ነው (ዕብ. 8፡10፤ ሮሜ 8፡9፤ ኤፌ. 3፡17)፤ ወደማንነታችን ውስጥ እርሱ የሆነውን ለመቅረፅ ከመንፈሳችን ወደልባችን በመንቀሳቀስ እግዚአብሔር ሕጉን በልባችን ላይ ይጽፈዋል (2ቆሮ. 3፡3)።

ሠ. ለዘላለማዊ መገለጡ የእርሱ ሙላት ለመሆን፣ የእርሱ መተለቅ የሆነ መጨመሩ እንሆን ዘንድ በውስጣችን ባለው መለኮታዊ ሕይወት ቅጽበታዊ በሆነው ሰው በማይቆጣጠረው አገልግሎት በኩል እግዚአብሔርን የማወቅ፣ እግዚአብሔርን የመኖር እና ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወቱና በባሕሪው እግዚአብሔር የመደረግ አቅም አለን—ኤፌ. 3፡16-21።

*© 2020 Living Stream Ministry*